# አገር እንዴት ሰነበች  ቁጥር 24

ሰኔ 26 ቀን 2014 ዓም(03-07-2022)

ከምን ጀምረን ከምን ላይ እንደምንጨርስ፣ከዬትስ ተነስተን ዬት ላይ እንደምንደርስ ስናስበው ግራ ይገባናል።ዘገባችን ሁሉ ያገራችንን የለት ተእለት ጉዞ የሚመለከት ስለሆነ በዬእለቱ ሳይሆን በዬሰዓቱ የሚለዋወጠው ያገራችን ሁኔታ መቋጠሪያውና መጨረሻው ያልታወቀ ቢመስልም ግን ሁኔታዎችና ችግሮች  እዬተባባሱ በመሄዳቸው በጊዜው መፍትሔ ካልተገኘለት ባገራችን አባባል "እርምጃውን አይተህ ማደሪያውን ገምት" የሚለውን ጥቅስ ብንጠቀምና ሂደቱን ብንፈትሽ  ጭራሽ ከለዬለት ደረጃ ላይ ሊደርስ እንደሚችል እርግጠኞች ሆነን ለመናገር እንደፍራለን።ይህንን ግምትና ፍራቻ እኛ ብቻ ሳንሆን ሌሎቹም ብዙሃን እንደሚጋሩት ከሚሰጡት አስተያዬት ተረድተናል።

የቀበኛው መንግሥት ነኝ ባይ የጎሰኞች ስብስብ  በለውጥ ስም ከራሱ ኢሕአዴግ ከሚባለው በረት ተገንጥሎ ኦሕዴድ በተባለው ሾፌር ሥልጣኑን ከተቆጣጠር ወዲህ ኦሮሚያ የተባለች የቅዠት ሃገር እመሠርታለሁ ብሎ በአገር ወዳዱ ሕዝብ  በተለይም በአማራው ማህበረሰብ ላይ የሚፈጽመው የማጥፋት ወንጀል ተጠናክሮ ቀጥሏል።በአማራው ላይም ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ላይ የሚፈጽመው ክህደት በእጥፍ እዬጨመረ መምጣቱን ባለፉት ቀናቶች ታዝበናል። የድርጅቶችንና የግለሰቦችን መቀያዬር እንደ ለውጥ አድርጎ የተቀበለው የዋህ ዜጋ ከአራት ዓመት መጃጃል በኋላ ዓይነጥላው ተገፎለት የተቃውሞ ጎራውን በመቀላቀል ላይ ይገኛል።እያጭበረበረ መሄድ ያልሆነለት፣ካርታው የተቃጠለበት የኦሮሙማው ቡድን በሕዝቡ ተቃውሞ በመደናገጥ ትክክለኛ ማንነቱን በሚወስደው የበቀል እርምጃ አሳይቷል።በሃይልና በማታለል ዕድሜውን ለማርዘም ቢሞክርም ከድጡ ወደማጡ እንጂ እንዳሰበው አልሆነለትም፤ሊሆንለትም አይችልም።

ከ15 ቀናት በፊት ከ2500 በላይ ንጹሃን የአማራ ተወላጆች በኦነግ ኦሕዴድ ጥምረት በወለጋ መጨፍጨፋቸውን ተከትሎ በውስጥና በውጭ አገር በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዘንድ በተለይም በአማራው ተወላጆች ዘንድ ትልቅ ቁጣንና ተቃውሞን ቀስቅሷል።በዬቦታው የሚካሄደው ሰልፍና ተቃውሞ ወንጀለኞች ላይ እርምጃ እንዲወሰድ፣ለሞቱት ወገኖች የመታሰቢያ የሃዘን ቀንና ሰንደቅ ዓላማ ዝቅ ብሎ እንዲሰቀል ቢጠዬቅም ከፓርላማ እስከ ክልሎች ባሉት የመንግሥት ተቋማትና ባለሥልጣኖች በኩል ለቀረበው ጥያቄ ተገቢ መልስ ከመስጠት ይልቅ በጠያቂዎቹ ላይ የአመጽ እርምጃ በመውሰድ ላይ ተሰማርተዋል። በተለይም አማራውን እወክላለሁ ብሎ ላለፉት 32 ዓመታት በአማራው ጫንቃ ላይ የተዘፈዘፈው ብአዴን የተባለ በድን  የምስለኔ ቡድን በአማራው ላይ የጥፋት ዘመቻ ከፍቶ ለብዙዎች መሞት፣መቁሰልና መታፈን ምክንያት ሆኗል።ቀደም ሲል ለ27 ዓመታት  ለወያኔ፣ ከአራት ዓመት ወዲህ ደግሞ ለኦሕዴድ ኦነግ መራሹ ጸረ ኢትዮጵያ ቡድን ታማኝ አገልጋይ ሆኖ በራሱ ሕዝብ ላይ ተነግሮና ተሰፍሮ የማያልቅ በደል ሲፈጽምበት ኖሯል፤አሁንም እዬፈጸመበት ይገኛል።ይህ የባንዶች ጥርቅም በሥልጣን ላይ እስካለ ድረስ የአማራው ማህበረሰብ ሙብቱ ታውቆለት ከሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ጋር በሰላምና በእኩልነት ይኖራል ማለት ዘበት ነው።የሌላውም ማህበረሰብ ተወላጆች እውነት በኢትዮጵያዊነታቸው የሚያምኑ፣ለእኩልነትና ለሰላም ፣ለፍትሕና ዴሞክራሲ መስፈን የቆሙ ከሆነ   በጫንቃቸው ላይ የተቀመጡትን የዬክልሉ ምስለኔዎች ማሶገድ ይኖርባቸዋል፤ ለተጨፈጨፈውም የአማራ ማህበረሰብ ወገናቸው ሊቆረቆሩና ከጎኑ ሊቆሙ ይገባል።በስማቸው የተኮፈሰው የሌቦች ስብስብ በነሱ ስም ቁማር እዬተጫወተ መሆኑን ሊረዱት ይገባል።ዛሬ በአማራው ላይ የተመዘዘ ቆንጨራ ነገ በነሱም ላይ ተራ በተራ ሊመዘዝ እንደሚችል መገንዘብና ለዚያ መከላከያ

የሚሆን ከአማራው ጋር ተባብረው ሕዝባዊ ሃይል መፍጠር ይኖርባቸዋል። አንዳንዶቹም የሚኖሩበትን መሬት ለመንጠቅ ሲባል እንደ አማራው በኦሮሙማው አሸባሪ ሃይል እዬተጨፈጨፉ ነው።ሌሎቹ ምንም አንሆንም ብለው ከተዘናጉ ነገ እሳቱ ሲለበልባቸው ቢጮሁ ሰሚ አያገኙም።የኦሮሙማው ጨካኝ ቡድን ተራ በተራ ሁሉንም ለመብላት አቅዶና ተዘጋጅቶ መንቀሳቀሱን ልብ ሊሉት ይገባል። በሰፈርና በክልል በጣጥሶ ካዳከመ በኋላ ሊውጥ የተዘጋጀ አውሬ መሆኑን ሊዘነጉት አይገባም።ለአናሳ ማህበረሰቦች አስቦና ተጨንቆ ሳይሆን አድቅቆ ለመሰልቀጥ መሆኑን መረዳት ከሚመጣው አደጋ ለማምለጥ መፍትሔ ለመፈለግ ይረዳል። ለመዳን ያለው ብቸኛ አማራጭ በኢትዮጵያዊነት ማማ ላይ ቆሞ ሃይልን አስተባብሮ የመጣውን የጋራ ጠላት መመከት ብቻ ሳይሆን ዳግም እንዳያንሰራራ ድባቅ መምታት ነው።

በሳምንቱ መጀመሪያ ላይ በአዲስ አበባ ከተማ  ሥራ ባለመግባት ሕዝባዊ ተቃውሞ ለማካሄድ ጥሪ ተላልፎ ነበር፤ሆኖም ግን ለጥሪው መልስ ከነዋሪው ሳይገኝ  ተቃውሞው በተማሪዎች ብቻ ተወስኖ ቀርቷል።ተማሪው በሚያስተላልፈው መፈክርና ጥሪ አትነሳም ወይ ፣ይኸ ባንዲራ ያንተ አይደለም ወይ?፤አትነሳም ወይ ስደት መገደል አይበቃህም ወይ?አትነሳም ወይ የፈሰሰው ደም ያንተ አይደለም ወይ?ለሚሉት መቀስቀሻዎችና ጥሪዎች  የመከራውና የጭቆናው፣የመፈናቀሉና ከሥራ የመባረሩ፣በኑሮ ውድነት የመጠበሱ ባለቤት የሆነው የአዲስ አበባ ኑዋሪ፣የልጆቹን ደም ሲፈስ እያዬ ምንም የማይሰማው ሆኖ ጭጭ ካለ እራሱን ለጨካኞች ካራ  አሳልፎ ለመስጠት እንደመረጠ ፣ወይም ኑሮው እንደተስማማው ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል።ፍርሃት እንዳይባል ፍርሃትም ድካና መጠን አለው።አጎብድጄ መኖር እችላለሁ ብሎም ከሆነ ማጎብደዱ በራሱ  ለአራጁ የተመቼ ሆኖ መገኘት እንጂ የአራጁን ልብ አያራራውም።ማረድ ልማድና ወግ ያደረገ የኦሮሙማው አውሬ ፍጡር የጭካኔው ደረጃ  እንኳንስ እወስደዋለሁ በሚለው ከተማ የሚኖረውን ቀርቶ በሆድ ውስጥ ያለን ሽልና የቀናት ዕድሜ ያለውን ጨቅላ አልማረም ።

የመንግሥትን ወራዳነትና ጸረ ሕዝብና ጸረ አገር ተግባር በመቃወም በተለያዩ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የሚካሄደው ተቃውሞ ወደ ሁለተኛና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመዛመት ላይ ሲሆን በባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ምግብ አንበላም በማለት ለተጨፈጨፉት ወገኖቻችን  አብሮነታቸውንና ሃዘናቸውን ገልጸዋል።ክልሉን የሚያስተዳድረው ምስለኔ ቡድን አማርኛ የማይናገሩ የሌላ ክልል በተለይም የኦሮሞ ክልል የጸጥታ ሃይሎችን አምጥቶ በራሱ ክልል ነዋሪ ላይ የሃይል እርምጃ ወስዷል። በዚህ የጨካኞች እርምጃ ብዙዎቹ ሲቆስሉ ብዙዎችም ታፍሰው ተወስደዋል።የሰልፉ አስተባባሪ ናቸው የሚባሉትንም አፍነው በመውሰድ ደብዛቸውን አጥፍተውታል።ቤተሰብ ዬት እንደደረሱ ሊያውቅ አልቻለም።በዚሁ በባሕርዳር ከተማ በተለያዩ ቦታዎች የጸጥታ ክፍል ባልደረቦች በተፈጸመ አሻጥር በአሸባሪዎች ቦምብ ተጣለ በሚል ሽፋን ወጣቱንና ተቃዋሚውን  ለማፈስ ሙከራ አድርገዋል።ይህ አይነቱ ዘዴ ሕዝብ አንቅሮ በተፋቸው መንግሥታት የሚፈጸም የተለመደ ስልት ነው።ሌላው ዘዴ በውጭ አገር ተወረርኩ በሚል ሽፋን ተቃውሞን ለማብረድ የሚደረገው አካሄድ ነው።በዚህ መልክ በሕዝብ ተቃውሞ የሚናጠው የሱዳንም ሆነ የአብይ መንግሥት ማምለጫ አድርገው ለመጠቀም የጦርነት ነጋሪት መጎሸማቸው አያስገርምም።እንደው ለይምሰል እንጂ የአብይ አህመድ መንግሥት ደፍሮ ከሱዳኖች ጋር ለኢትዮጵያ ልዑላዊነት ሲል ይዋጋል ማለት ሞኝነት ነው።ገና ሲጀመር መሬቱን ቆርሰው እንዲወስዱ ፈቃድ የሰጠው አብይ ነው።ለዚያም ማረጋገጫው በሱዳኑ ወታደራዊ መሪ አብዱል ፋታህ አል ቡርሃን ወረሩ ተብለን ነው ከሚለው ቃል በተጨማሪ ላለፉት ሁለት ዓመታት ያስቆጠረ ወረራ በዝምታ ማለፉና አሁንም ለመዋጋት አንሻም፣በድርድር እንፈታዋለን የሚል የመንበርከክ መልእክት ማሰማቱ ነው።ኢትዮጵያ መንግሥት  አልባ በመሆኗና በውስጥ ውዝግብ በመተራመሷ የልብ ልብ የተሰማት ሱዳን ሌላ መሬት ይቀረኛል በማለት እዬፎከረች ሲሆን የግድቡንም

ሥራ ለማስተጓጎል ስልት ነድፋ በመንቀሳቀስ ላይ ነች።የወያኔ ከሃዲ ቡድን የገዛ አገሩን በመውጋት ከጎኗ ተሰልፏል።ድንበር ላይ የሚዋደቁት የከባቢው ነዋሪዎች የሆኑት አማራዎችና ፋኖዎች ብቻ ናቸው። የመከላከያ ተብዬው በቦታው ድርሽ አላለም።የተጠመደው ፋኖንና የአማራውን ሚሊሽያና ልዩ ሃይል በማሳደዱ ላይ ነው።በሱዳን ወራሪ ጦር ላይ ጥይት ለመተኮስ ያልደፈረው በተረኞች የሚታዘዘው መከላከያ ተብዬው በኢትዮጵያውያን ላይ በጦር አውሮፕላንና በከባድ መሣሪያ ሳይቀር ጥቃት ከመፈጸም አልቦዘነም።የአማራው ትግል ግን እንደቋያ እሳት እዬተቀጣጠለ በመሄድ ላይ ነው።

በደብረብርሃን፣በጎንደር በሸዋሮቢት እንዲሁ የተማሪዎቹ እንቅስቃሴ ማህበረሰቡን እዬሳበ መጥቷል። በተለይም በሸዋ ሮቢት ተማሪውና ሕዝቡ በነቂስ ወጥቶ አብይ አህመድንና የሚመራውን ብልጽግናን ከማውገዝም ባለፈ አብይና አጋሮቹ የብልጽግና ጀሌዎች ከሥልጣን እንዲወርዱ፣የታፈኑትም እንዲለቀቁ ጠይቋል። ለተጨፈጨፉት የአማራ ተወላጆች ሰንደቅዓላማ ዝቅ አድርገው ሰቅለዋል። በዚህ ግብግብ የመንግሥት ሃይል ተኩስ ከፍቶ ንጹሃን መገደላቸውና መቁሰላቸው ተሰምቷል።እንቅስቃሴው ምህዳሩን አስፍቶ በማጀቴም ተመሳሳይ የሕዝብ ተቃውሞ ተካሂዷል። በደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ የተካሄደውን የተማሪዎች ተቃውሞ ለዬት የሚያደርገው ተቃውሞ ይነሳል በሚል ፍርሃት ዩኒቨርሲቲው በማታ ላይ በታጠቁ ወታደሮች ተከቦ መሪዎችን ለማፈን ሲሞክሩ ተማሪው ከዳር እስከዳር ተጠራርቶ ከመጡት አፋኞች ጋር ግብግብ መግጠሙ ነው።በዚህም ብዙ ተማሪዎች የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል።በጣም የሚያናድደው ንፁሃን መጨፍጨፋቸውን በሚቃወም ብዙሃኑ ውስጥ ጭፍጨፋውን የሚደግፉ ከመንግሥት ጎን ተሰልፈው አሳልፈው የሚሰጡ የአማራው ተወላጅ የሆኑ ጥቂት ባንዳዎች መኖራቸው ነው።በነዚህ ላይ እርምጃ መውሰድ ለትግሉ ውጤት ወሳኝ ነው።

የከሃዲና የባንዳዎች መኖር በሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች የሚታይ ስለሆነ ብዙም ሊደንቀን አይገባም።የኪነት ሰዎች፣ጋዜጠኞች፣መምህራን---ወዘተ ከሕዝቡ ጎን የቆሙ እንዳሉ ሁሉ ከጨፍጫፊዎችም ጋር የተሰለፉ መኖራቸውን አይተናል።ምሳር ካለጠማማው የእንጨት እጀታ ዛፍ እንደማይቆርጥ ሁሉ ጠላት ካለነዚህ ጠማማ ሆድ አደሮች ትብብር ያሰበው አይሳካለትም።እነዚህ ሆድ አደሮች የሚያገለግሉት ቡድን ሲወድቅ አብረው ይወድቃሉ።አወዳደቃቸው የከፋ የሚሆነው በጸረ ሕዝብነት የቆሙበት ቦታ ሜዳ ሳይሆን ጅው ያለ ገደል አፋፍ በመሆኑ ነው።

ከውድቀቱ የማይማረው የኦሮሙማው ስብስብ በዚህም ሳምንት በተለያዩ ትምህርትቤቶች ግቢ ውስጥ የኦነግን ባንዲራ ለማንጠልጠልና የቄቤን መዝሙር ለማዘመር ያደረገው ሙከራ በተማሪዎቹና በመምህራኑ እንዲሁም በወላጆችና በነዋሪው ሕዝብ ተቃውሞ ሊከሽፍ ችሏል።ባንዲራውም ተቀዳዶ ተጥሏል።

ከተማሪዎች ተቃውሞ ወጣ ስንል በባሕርዳር ከተማ ከዬቦታው የመጡ የፋኖ መሪዎች ትግላቸውን በአንድ ዕዝ ሥር ለማካሄድ ውይይት ለማድረግ በተሰበሰቡበት ቦታ የክልሉ ጦርና አፋኝ ቡድን ከበባ አድርጎ እንደታፈኑ ተሰምቷል።የፋኖ ተወካዮችን የክልሉ አመራር ከፋኖ መሪ ከዘመነ ካሴ ጋር አደራድሩን በማለት ከቀረቧቸው በኋላ የተፈጸመ ክህደት መሆኑ ተገልጿል።ብአዴንን አምነው መሃል ከተማ መሰብሰባቸውን ስንሰማ ምናልባት በብአዴን የተደራጁ ፋኖዎች ይሆናሉ እንጂ ብልጽግናን በተለይም ባእዴንን አሶግዳለሁ ብሎ የሚታገል፣ ከነዘመነ ካሴ ጋር ንክኪ ያለው ፋኖ እንዲህ አይጃጃልም ከሚል ላይ እንድንደርስ ተገደናል።የሚታገሉትን ሃይል ያሶግዱታል እንጂ አምነው ሊደራደሩትና የቃልኪዳን ቀለበት ሊያስሩለት ቀርቶ ሊደመስሱት ካልሆነ በቀር ባለበት ድርሽ አይሉም።ፋኖን ፋኖ የሚያሰኘው በከተማ ሳይሆን በገጠርና በጫካ የሽምቅ ውጊያ በማካሄዱ ነው።ወደ ከተማ ቢገባም ጠላትን አጥቅቶ ለመሰዎር ወይም ለማምለጥ(Hit and Run)ግዳጅ ነው።ስለሆነም

በከተማ ውስጥ እዬተንንባለለ በሆቴል አዳራሽ ውስጥ ስብሰባ አይቀመጥም።እንዲህ አይነት ስህተት ተፈጽሞ ከሆነ እንዳይደገም ለማሳሰብ እንወዳለን።

ሱዳን የኢትዮጵያን ድንበር ተሻግራ ወታደሮቼ ተገለዋል በሚል ሽፋን አገራችንን ለመውረር ወታደሮቿን በድምበር ላይ ስታሰልፍ፣ብሎም በተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክርቤት በኩል ክስ ስትመሰርት የኢትዮጵያ መንግሥት ነኝ ባይ ቡድን ተገቢውን ምላሽ ከመስጠት ይልቅ በመለማመጥና በሞቱት ወታደሮች የሚጠዬቁት ሌሎች ኢመደበኞች ናቸው፣የመከላከያ ሃይል በቦታው የለም ሲል በአማራ ፋኖና በሚሊሽያ ላይ ጣቱን ቀስሯል።ይህ ማለት የሁለቱንም አገራት ሰላም የሚያደፈርሱት በአካባቢው የሚኖሩት አማራዎች ናቸው ለማለት ነው።ከዚህም ቀደም ሲል ለከባቢው ሰላም እንቅፋት የሆኑት አማራዎች ናቸው የሚል ውንጀላ ሰንዝሮ እንደነበር አይረሳም።በአገር ውስጥ የዜጎችን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ ያልቻለ ቡድን በውጭ የሚመጣን ወራሪ ለመከላከል ወኔና ፍላጎት እንደሌለው በተደጋጋሚ ታይቷል። ይባስ ብሎም ለተጨፈጨፉት የራሱ ዜጎች ያላዘነ ለመውረር ለመጡ ለሱዳኖቹ ወታደሮች መሞት የሃዘን መልእክት መላኩ ሲታይ ምን ያህል ለኢትዮጵያውያኖችና ለኢትዮጵያ ደንታቢስ መሆኑን ያረጋግጣል።የብልጽግና ተብዬው ስብስብ በሥልጣን ላይ እስከቆዬ ድረስ ከዚህ የከፋም ክህደት ሊፈጽም ይችላል።

በሕዝብ ተቃውሞ የሚናጠው የሱዳን የወታደራዊ መንግሥት በኢትዮጵያ ተወረርኩ፣ወታደሮቼ ተገደሉ ብሎ ቢለፍፍም የሱዳን የሕዝብ ተቃውሞ ሊቀለበስ አልቻለም።እንደውም ይባስ ብሎ ከዳር እስከዳር መላ አገሪቱ በሕዝባዊ ተቃውሞ በመናጽ ላይ ነች።መንገዶች ተዘግተው ወደዋና ከተማዋ ካርቱም ለመግባት አልተቻለም።ይህ አይነቱ ሕዝባዊ ተቃውሞ ለሱዳን ሕዝብ እንግዳ አይደለም።ምንም ከባድ መስዋዕትነት ቢከፈልም የሚቃወማቸውን መንግሥታት ከሥልጣናቸው የማባረር የካበተ ልምድና ድፍረት አለው።ከመጀመሪያው የሱዳን ፕሬዚዴንት ከኢብራሂም አቡድ ጀምሮ ፣አልማህዲ፣ኑሜሪና አልባሽር ድረስ ከሥልጣን የወረዱት በሕዝባዊ ተቃውሞ ነው።የዚህም ወታደራዊ አምባገነን እጣ ፈንታ ከቀድሞቹ የተለዬ አይሆንም።በጣም የሚገርመው ያለፉት ተቃውሞዎች መነሻ ሱካር መሆኑ ነው።የአሁኑን ለዬት የሚያደርገው የዳቦ ጥያቄ ማንሳቱ ነው። ታዲያ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄ ጋር ሲያስተያዩት የሱዳኖቹ የቅንጦት ይመስላል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በአገሩ በሰላምና በእኩልነት እንዳይኖር፣እርስ በርሱ የሚያባላና የሚያጫርስ፣አገር የሚያፈርስ ቡድን የፈለገውን ሲያደርግ፣ሃይማኖትና በጎሳ ማንነቱ እዬለያዬ ሲገል ሲያፈናቅል፣ጎልማሳና ሽማግሌ ብቻም ሳይሆን ጽንስና ጨቅላ ሕጻናትን ሲያርድ እንደሱዳኖች ሥርዓቱን ለመለወጥ ሆ ብሎ አለመነሳቱን ሲያዩት በሕዝቡ ላይ የወረደ አዚም ወይም ከላይ የተነሰነሰበት እርግማን ይኖር ይሆን ብለን ለመጠዬቅ እንገደዳለን።መሪ በማጣትም ሳይሆን መሪዎቹን አሳልፎ በመስጠት መሆኑ ደግሞ ይበልጥ የሕዝቡን ስነልቦና እንድንመረምረው ይገፋፋናል።መሪዎቹን የሚያወድሰው ከሞቱ በኋላ መሆኑ ደግሞ የሕብረተሰቡን ልቦና ለማወቅ የሚደረገውን ጥረት ውስብስብ ያደርገዋል።ከኢትዮጵያ ሕዝብ በላይ መከራ ያዬ፣የተራበ፣የተሰደደ፣የታረደ፣በጥይት የተቆላ፣በሳት የነደደ ሕዝብ በዓለማችን ላይ መኖሩ ያጠራጥራል።አሁን ላይማ ኢትዮጵያዊ ነኝ ለማለት ቀርቶ የኢትዮጵያ ጎረቤት አገር ሰው ነኝ ለማለት የሚሸማቀቁበት ጊዜ ላይ ደርሰናል።በቀድሞ አባቶቻችን ትግል የተጎናጸፍነውን ክብርና ነጻነት በእኛው እኩይ ትውልድ ተገፈን መሳቂያ መሳለቂያ ሆነናል።ብሔራዊ ኩራት በራስ ወዳድነትና ስግብግብነት ተቀይሮ እንኳንስ ለአገር ለወለዱትም ልጅ የማይራራ የእጥፍ አንጀት ባለቤቶች ሆነናል። ጥቂት አገር ወዳዶች ቢኖሩን እነሱንም ለማዳን ሳይሆን ለማስጠቃትና ለማጥቃት እንሯኳከራለን። አሳልፈን በመስጠት የግዳይ ጥሎሽ ለማቅረብ እንወዳደራለን።ታዲያ እንዴት አድርገን የሰላም፣ የእኩልነት ፣የነጻነትና የአገር ባለቤቶች እንሆናለን?ከአውሬ በታች ማነነታችንንና ድክመታችንን አምነን

ሰው ለመሆን የምንችልበትን መንገድ መከተሉ እድገትና ብልጽግናው ቢቀር በሌላው የዓለም ማህበረሰብ  በተለይም በአፍሪካውያን ዘንድ የነበረንን ተቀባይነት መልሰን ልናገኝ እንችላለን።ባለቤት ያቀለለውን አሞሌ ባለዕዳ አይቀበለውም ነውና በሌሎች ለመከበር እራሳችንን ማክበር ይገባናል።በእኛ ታሪክና ሰንደቅ ዓላማ ሌሎች ሲኮሩ የአገርና የሰንደቅ ዓላማው እንዲሁም የቋንቋውና የፊደሉ ባለቤት የሆነው አንዱ አካላችን በራሱ ላይ ሸፍቶ የባርነትን ጎዳና መርጧል።በዚህ የተሳሳተ መንገድ የሚነጉደው ማህበረሰብ ከአገራችን ጠላቶች በኩል ድጋፍ ቢኖረውም የነሱ ድጋፍና እውቅና አገሩን እስኪያፈርስላቸው እንጂ ከዚያ በኋላ እሱንም እንደ ከብት ለጉመው እንደሚጠቀሙበት ልብ ሊል ይገባል።አንዱ ጠፍቶም ሌላው ሊኖር እንደማይችል መረዳት አለበት።

የማን ቤት ፈርሶ የማን ሊበጅ፣

ያውሬ መፈንጫ ይሆናል እንጂ።

የሚለውን የማስጠንቀቂያ ደወል ቢያደምጡት ይጠቅማል እንጂ አይጎዳም። አጥፍቶ ከመጥፋት ያድናል።

የኦሮሙማው የጭካኔው አንዱ መግለጫ በኦሮሞ አውሬዎች የተጨፈጨፉት የአማራው ተወላጆች ዓይናቸው ሳይፈስ  አጫሉ ሁንዴሳ  የተባለው በራሳቸው በኦሮሞዎች በተገደለው የኦሮሞ ዘፋኝ ስም የተቋቋመው ድርጅት ያዘጋጀው የዘፈን ዝግጅት መካሄዱን ስንሰማ ለጭካኔያቸው ማሳያና ለጨፍጫፊዎቹ ድጋፍ ሆኖ ተሰምቶናል።ምንም እንኳን እንደ ሰው ሟቹ ሃጫሉ በግፍ በመገደሉ የምናዝን ቢሆንም በሱ ስም ለመጠቀም የሚሞክሩትን ጨካኞች እንጂ ግለሰቡን ቀላቅለን አናይም። መልካምም ሆነ በጎ ታሪክ ቢኖረውም እሱ አንድ ጊዜ ሞቷል።ከመቃብሩ በላይ የሚኖረው ሥራው ነው።እንደ አገራችን ባሕልማ ቢሆን ኖሮ እንኳንስ ሕዝብ አንድ የጎረቤት ሰው ከሞተ ለተወሰኑ ቀናት በሙዚቃ መጨፈር ቀርቶ ራዲዮ አይከፈትም ነበር።በዛ አስከሬን ሲያልፍ ቆሞ እጅ መንሳት ልማዱ በሆነ ሕዝብ በኖረበት አገርና መሬት የሰው ልጅ በጭካኔ ተጨፍጭፎ ለመቃብር ሳይበቃ ለአውሬ ሲሳይ ሲሆን ከምናይበት ጊዜ ላይ መድረሳችን በጊዜው ሳይሆን በእኛው ልናዝንና ልናፍር ይገባል።ጊዜ ሰው በመረጠው ጎዳና  የሚተላለፍበት የህይወት መንኮራኩር እንጂ ሰውን ጠፍጥፎ አይሠራም።ጊዜ ትናንትም ዛሬም ነገም ያው ነው።ነበር፣አለ፣ይኖራልም።በጊዜ መጠቀምና በታሪክ ተመስግኖ ወይም ተወግዞ ለመኖር ወሳኞቹ እኛው ነን።

የኦሮሞዎቹ ዳንስና ዳንኪራ ሲገርመን ሌላው በእግርኳስ ጨዋታ ሰበብ ጎራ ለይቶ ሲነታረክና ሲጨፍር፣በአስረሽ ምችው ድግስ ገንዘቡን፣ጊዜውንና ጉልበቱን ሲያፈስ ማዬቱ ስለአገር መኖር የሚገባው ስሜት ገደል መግባቱንና የእብደት፣የጭካኔውና፣የራስ መውደዱ መጠኑ ጣራ መንካቱን እንገነዘባለን። የትኛውም ትውልድ በታሪክ ሚዛን የሚለካውና የሚፈረጀው ባሳለፈው ተግባሩ ስለሆነ የዛሬውም ትውልድ እንዲሁ በዛሬው ምግባሩ ይፈረጃል።የዛሬው ትውልድ የትናንትናውን በመርገምና በመከሰስ ወይም በማወደስ  በነገው ትውልድ ሚዛን ላይ ሳይቀርብ የሚያልፍበት ዕድል የለውም። እሱም በተራው ይፈተሻል።

በአብይ አህመድ የሚመራው የኦሕዴድ ኦነግ መራሹ ቡድን በአማራው ላይ የመዘዘው ሳንጃ ወደ አፎቱ አልገባም።በዬጊዜውና በዬቦታው ይበልጥ እዬተሳለ እንጂ እዬዶለዶመ አልሄደም።በወሊጋና በጋምቤላ ብሎም በቤንሻንጉል በኩል አማራውን ከቦ ለመምታት ከሚያደርገው ተደጋጋሚ ጥቃትና  ሴራ በተጨማሪ በሥልጣን ጥያቄ ሲነታረክ ከነበረው ጠፍጥፎ ከሠራው ከወያኔ ጋር ለመታረቅ የወልቃይትንና ራያና አዘቦን የአማራውን መኖሪያ ለም መሬት አሳልፎ ለመስጠት በስብሰባ ወስኖ እዬተንቀሳቀሰ መሆኑን ይፋ አድርጓል።ወያኔ ከ32 ዓመታት በፊት በጉልበት የያዘውን መሬት ከሶስት

ዓመት ወዲህ ባለቤቱ የሆነው አማራው በጉልበቱ ማስመለሱን ተከትሎ በተደጋጋሚ በወያኔ የተደረገው ሙከራ ባለመሳካቱ አሁን ለኦሕዴድና ለወያኔ የእርቅ ጭዳ ሆኖ ቀርቧል።ሕገመንግሥት ሳይኖር በሕዝበ ውሳኔ ያልወሰዱትን መሬት አሁን በሕገመንግሥቱ መሠረት በሕዝበውሳኔ ይሰጣቸው ብሎ ማለቱ በሕግም በታሪክም ያልተደገፈ አማራውን ለማዳከምና ለማጥፋት የታቀደ ክህደት ነው። የአማራው ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለፍትሕና ለሃቅ ቆሜያለሁ የሚል ዜጋ በተለይም የትግራይ ተወላጅ በታሪክ ላለመጠዬቅና ትውልዱ ከሃዲና ወራሪ ተብሎ እንዳይጠራ ሕይወቱን ገሃነም ያደረጉበትን ሕወሃት የተባለ ድርጅትና መሪዎቹን ከጫንቃው ላይ አውርዶ ሊጥላቸው ይገባል።በውሸት ትርክት ተታሎ ከእኩይ አድራጎት እንዲታቀብ ጥሪ እናደርጋለን።ታሪክ ይከበር ስንል በወልቃይትና በራያ መሬት ላይ የትግሬም ሆነ የሌላው ጎሳ ተወላጅ አይኑር ማለት አይደለም።እንደ ጥንቱ ሁሉም ዜጋ አገሬ ብሎ ከፈለገበት ቦታ ሄዶ ለመኖርና ሃብት የማፍራት መብትና ነጻነት እንዳለው እውቅና በመስጠት ነው።የትግራይ ተወለጃ ከወያኔ በፊት ወልቃይትና ራያ ውስጥ ከነባሩ ሕዝብ ጋር አብሮ በሰላም ኖሯል።ወደፊትም ሊኖር ይችላል።እንዳይኖር የሚያደርጉት በስሙ የሚነግዱት አገር ጠሌዎችና የባዕዳን ተላላኪዎች ናቸው።ይህንን በጽሞና ሊረዳው ይገባል።በወገኑ በአማራው ላይ ከመዝመት በራሱ አሳሳቾች ላይ እጁን እንዲያነሳና የገነባት አገር፣ የኢትዮጵያ ባለቤትነቱን ማስከበር አለበት እንላለን።

ለውጥ ስንል አንዱ ጎሳ በሌላው ጎሳ እዬተተካ አገርና ሕዝብ በጎሳ ሽክርክሪት ውስጥ ተዘፍቀው እርስ በርስ እዬተጋደሉ ይኑሩ ማለት ሳይሆን፣ሁሉም ሕዝብ በኢትዮጵያዊነቱ ተከባብሮና ተስማምቶ በሰላም የሚኖርበት ሥርዓት ይዘርጋ ማለታችን ነው።ዜጋ በፈለገው ቦታ ኖሮ ሃብት ንብረት የማፍራት መብቱ ይጠበቅለት ማለታችን ነው።በሃገሩ ጉዳይ ላይ ሕዝብ ይወስን ማለታችን ነው።ዜጋ የመምረጥና የመመረጥ መብቱ ይከበርለት ማለታችን ነው።ሕዝብ የመቃወምና የመደገፍ መብቱ ይከበርለት ማለታችን ነው።አሸባሪና ከፋፋይ ይወገድ፤ለፍርድም ይቅረብ ማለታችን ነው።የሃይማኖትና የቋንቋ ልዩነት የሚጠቀሙበትና የሚጎዱበት መስፈርት አይሁን ማለታችን ነው። ሙስናና አድልኦ ይወገድ ማለታችን ነው።ሁሉም የሚግባባበት የሚናገርበትና የሚጽፍበት በራሱ ፊደል የዳበረ አንድ የጋራ ቋንቋ ይኑር ማለታችን ነው።ለሁሉም ጌጥና ክብር የሆነ የሚታወቅበት አንድ ታሪካዊ ሰንደቅ ዓላማ ይኑረው ማለታችን ነው። ሰንደቅ ዓላማውንና ቋንቋውን በተመለከት ሌላ አዲስ ፍለጋ ላይ እንሂድ ማለታችን ሳይሆን የጠቀመንን የነበረና ያለንን አማርኛችንና አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ሰንደቅ ዓላማችንን ከፍ አድርገን ብንይዘው ከኛም አልፎ ለመጭው ትውልድ መኩሪያ ይሆናል።በጦር ሜዳ ላይ ውሎ የድል ምልክት የሆነው ሰንደቅ ዓላማችንን የሚጠሉት በጦር ሜዳ የተሸነፉት ጠላቶቻችንና የረጅም ዕድሜ ባለቤት የሆነ ባንዲራ የሌላቸው ናቸው።ሌሎቹም የነጻነት ምልክትነቱን ተቀብለው የቀለሙን አቀማመጥ ብቻ በመቀያዬር የራሳቸው ሰንደቅ ዓላማ ያደረጉ አገሮች ብዙዎች ናቸው።

በጋዜጠኞችና በተቃዋሚዎች ላይ በሚደረገው ማሳደድ ላይ ሌላ ተጨማሪ ውንብድና መከሰቱን ታዝበናል።የታሠሩት ይፈቱ የሚለውን የሕዝብ ጥያቄ የመለሱ መስለው በስኳድርባ ሌላ አፈና ማካሄድ የሰሞኑ የብልጽግና ጥበብ ሆኖ ታይቷል።በአማራው ክልል በብአዴን የታሠሩትን ፍርድ ቤት በገንዘብ ዋስትና ሲፈታ ገንዘቡ ከተከፈለ በኂላ እስረኞቹ ከእስርቤት ሲወጡ እበር ላይ ጠብቆ የሚያስር ሌላ የፍዴራል አፋኝ መድቦ ለዳግም እስር መውሰዱ ጋር ተያይዞ የባልደራሱ ስንታዬሁ ቸኮል የዚህ ሰለባ ከሆኑት አንዱ ሆኗል።እስከአሁን የገባበት አይታወቅም።ሌሎቹም በስበብ ባስባቡ ሳይፈቱ ቀርተዋል። ታዲዮስ ታንቱም እንዲሁ ከፍርድ ቤት ውሳኔ ውጭ እዬተሰቃዬ ነው።ተመስገን ደሳለኝ በተደጋጋሚ ዳኛ የለም በሚል ሰበብ በመመላለስ የስቃይ ጊዜውን እያረዘሙበት ነው።ሌሎቹም በጠራራ ጸሓይ ታርጋ በሌላቸው መኪናዎች በሚንቀሳቀሱ አፋኞች እዬታፈኑ የገቡበት ያልታወቀው ብዙዎች ናቸው። ከነዚያም ውስጥ በሰላ ብዕሩ የሚታወቀው ገጣሚ ወጣት በላይ በቀለ ወያ አንዱ ነው።እስከአሁን የገባበት ባለመታወቁ አሮጊት እናቱና ሽማግሌ አባቱ፣እህቱና ቤተሰቡ በጭንቅና በሃዘን ላይ ወድቀዋል።

ከእንዲህ አይነቱ የወሮበሎች አፈናና ካለንበት ቀውስ ለመውጣት ከላይ የደረደርናቸውን የሕዝብ ፍላጎቶች እውን የሚያደርግ ከሕዝቡ ለሕዝቡ፣የሕዝቡ የሆነ መንግሥት መኖር አለበት።ያንን ቋሚ መንግሥት ለመመስረትና ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የሚረዳ የሽግግር መንግሥት መቋቋሙ የግድ ይላል።

ትግላችን ለዚህ የመጨረሻ ግብ የሚያደርሰን እንጂ በጥገና ለውጥ ተታሎ የሚሰናከል ወይም ለተወሰኑ ቀናት አደባባይ ላይ ወጥቶ በመጮህ የሕይወት ዋጋ ተከፍሎበት የሚበተን መሆን የለበትም።የዓላማ ጽናትና ሙሉ ዝግጅት ሊኖረን ይገባል።በዬቦታው የተነሳሳው የሕዝብ እምቢተኛነት ከግብታዊነት ወደ ቀጣይነት እስከድል ድረስ የሚመራ አካል መፈጠር አለበት።የፖለቲካና የወታደራዊው ትግል ካልተቀናጀ ለጠላቶቻችን የተመቸን እንሆናለን።የእኛ መዝረክረክና በአንድ አለመቆም የጎሰኞቹ ስብስብስብ አገር የመበተኑን ዓላማውን በቀላሉ ለመፈጸም ያስችለዋል።ካልተደራጀን አገር የማፈራረሱን ግማሹን ሥራ የምንሠራለት እኛው እንሆናለን።

ሕዝባዊ ትግሉን የሚመራ አካል ይፈጠር!

ብልጽግና ተወግዶ የሽግግር መንግሥት ይቋቋም!!

በንጹሃን ዜጎች ላይ ጭፍጨፋና ወንጀል የፈጸሙ ይቀጡ!!!

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘላለም ትኑር!!!!